# የታል ክብር ለካህኑ

ክብርን ስንሰጥ
ለሰዓሊው ለደሃፊው
ለከያኒው ለደራሲው
ለእስፖርተኛው ለኳስ ምሁር
ለአቀንቃኙ ለዲሳይነር
ለአርኪቴክቱ ለዶክተሩ
ለምሁሩ ለሰርጂኑ
የታል ክብር ለካህኑ

ተቀበሉ ሹመት ክብር
ሊኖሩባት በዓለም ምድር፡፡
ዓምላክ ያለው በአንደበቱ
እንድንገኝ በአክብሮቱ፡፡
ክብርማ አለው እንጂ !
በድኑን ሕብስት በደሎቱ ሕይወት ሰጥቶት
በጣቶቹ በእጆቹ አበጃጅቶት፡፡
ከባድ እንጂ የኔ መባል
ያውም የአምላክ የመለኮት የዕሳት አካል፡፡
ይላቸዋል ምርጥ ዕቃዎች
አሰብናቸው ተራ ሰዎች?
ዓይኔ ናቸው ብርሃኔ
አትንኩብኝ ስለእነሱ አለሁ እኔ፡፡

እንኳን አምላክ በመንበሩ
የሾመውን ይሁን ብሎ
ይከበራል የሰው ሹመት
የምድሩ ዓለም ያለንበት፡፡
ቢመርጥ ከገሊላ የተናቀ
ምስጢር የእሱ የረቀቀ፡፡
እሱ ቢመርጥ መግደላዊት
የተናቀች የረከሰች ሰው የጠላት፡፡
ለመጠየቅ እሱነቱን
ፍቅርን ሊሰጥ አንድም ሳይመርጥ፡፡
አለው ነገር ሲሰጥ ቦታ
በችሎታው በስልጣኑ
በኖረበት በዙፋኑ፡፡

አላቀ እንጂ አበለጠ!
የታሰረ ላይፈታ
ካለእነሱ ላይረታ
ካልተሾኘ ይቅር ብለው ሳይታጠብ በደሎቱ
መላም የለው ሁሉም ከንቱ፡፡

እኛስ ሰዎች ስንል ችላ
ወረድ ወረድ ገፋ ገፋ መከባበር ወደሁዋላ
መቅረዛችን እንዳይጠፋ
መክሊታችን እንዳይሰፋ፡፡

በሹመቱ ጥልቅ ብለን
እንዳልሆነ ካደረግን
የቀደሰን ካረከሰን
መቸም አምላክ ቸር ነው እና በቸሮታው ይታደገን፡፡

ተቀበሉ ሹመት ክብር
ሊናዙባት በዓለም ምድር
ዓይኔ ናቸው ብርሃኔ
አትንኩብኝ ስለእነሱ አለሁ እኔ፡፡

በቀደደው ውሻ አጥሩን
ሳናስገባ አውሬ ጅቡን
ችግር ቢኖር ተመካክረን፣ ተደማምጠን
ሳናስወጣው በር ከፍተን
በሰውነት ተከባብረን
የጎደለን አስተካክለን
መከባበር ባህላችን
ባናዳምጥ ባንሰማም ከዓምላካችን፡፡
መከባበር ዋጋ አይጠይቅ ብር መምዘዝ
ውጣ ውረድ የሌለበት የለው መዘዝ፡፡
በደመነፍስ የሚሰራ አይደል ተረት
ተዋህዶ ከደም አጥንት፡፡
መከባበር ሰው ለይቶ ለፈገግታ
መሆኑ ነው ሥነ ምግባር የታይታ
ዓምላክ ቸሩ ይጠብቀን
በይቅርታው በትዕግሥቱ ያስተካክለን፡፡

ተቀበሉ ሹመት ክብር
ሊናዙባት በዓለም ምድር
ዓይኔ ናቸው ብርሃኔ
አትንኩብኝ ስለእነሱ አለሁ እኔ፡፡

ከማቲዮስ ወንጌል 16፣ 13 — 12 እና
ከቤተ ክርስቲያናችን ከከበሩ መዳሕፍት ተወስዶ
በወ/ት አፎሚያ ሚካዔል ተዘጋጀ
ሚያዚያ 2000 ዓ:ም